## ትምህርት 44

1. ዘካርያስ በቤተ መቅደስ ውስጥ ሳለ ምን ሆነ?

ሀ- የእግዚአብሔር መልአክ ለዘካርያስ ተገለጠለት።

2. መልአኩ ለዘካርያስን ምን አለው?

ሀ- መልአኩ እግዚአብሔር ለዘካርያስ ልጅ እንደሚሰጠውና የልጁም ስም ዮሐንስ እንደሚባል ነገረው።

3. ቀጥሎስ መልአኩ እግዚአብሔር ለዘካርያስ ስለሚሰጠው ልጅ ምን አለ?

ሀ- መልአኩ የዘካርያስ ልጅ ዮሐንስ ሕዝቡን ለሚመጣው አዳኝ ያዘጋጃል አለ።

4. መልአኩ የሚመጣውን አዳኝ ማን አለው?

ሀ- ጌታ።

5. ጌታ ማን ነው?

ሀ- እግዚአብሔር።

6. መልአኩ ለማርያም ምን ነገራት?

ሀ- መልአኩ ማርያም የሚመጣውን አዳኝ እንድትወልድ እግዚአብሔር እንደመረጣት ነገራት።

7. የማርያም ልጅ ስሙ ማን ይባላል?

ሀ- ኢየሱስ።

8. «ኢየሱስ» ማለት ምን ማለት ነው?

ሀ- «ኢየሱስ» ማለት አዳኝ ወይም ታዳጊ ማለት ነው።

9. መልአኩ የማርያም ልጅ የልዑል ልጅ ይባላል ሲል ምን ማለቱ ነው?
ሀ- የማርያም ልጅ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ማለቱ ነው።

10. የማርያም ልጅ የእግዚአብሔር ልጅ የሚሆነው እንዴት ነው?
ሀ- እግዚአብሔር አብና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ወልድን እንደእግዚአብሔር ልጅና እንደሰው ልጅ ወደ ምድር ስለ ላኩት ነው።

11. የማርያም ልጅ አምላክ ወይስ ሰው ነው?
ሀ- የማርያም ልጅ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ነው።

12. የማርያም ልጅ ያለሰው አባትና እናት የዘር ፍሬ የተወለደው ለምን ነበር?
ሀ- የአዳምና የሔዋን ኃጢአት ሳይኖርበት እንዲወለድ።
ለ- ያለ ኃጢአት ፍጹም ሆኖ እንዲወለድ።

13. ኢየሱስ እግዚአብሔር ለአብርሃም ለይስሐቅ፥ ለያዕቆብና ለሰዎች ሁሉ ቃል የገባው አዳኝ ነው?
ሀ- አዎን።

- የዘካርያስ ሚስት ኤልሳቤጥ ልጅ የምትወልድበት ጊዜ ደረሰ።

ሉቃስ 1፡57-58

57- የኤልሳቤጥም የመውለጃዋ ቀን ደረሰ፤ ወንድ ልጅም ወለደች።
58- ጎረቤቶቿና ዘመዶቿም ጌታ ታላቅ ምሕረት እንዳደረገላት
ሰሙ፤ የደስታዋም ተካፋዮች ሆኑ።

- እግዚአብሔር ለዘካርያስና ለኤልሳቤጥ ልጅ ለመስጠት የገባውን ቃል ፈጽሞአል?

- አዎን።

- እግዚአብሔር ለዘካርያስና ለኤልሳቤጥ ልጅ ሰጣቸው ስሙንም ዮሐንስ አሉት።

- የዘካርያስ ልጅ ዮሐንስ በተወለደበት ጊዜ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በዘካርያስ በኩል ተናገረ።

ሉቃስ 1፡67-71

67- የሕፃኑም አባት ዘካርያስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ እንዲህ ሲል ትንቢት ተናገረ፤

68- «የእስራኤል አምላክ፣ ጌታ ይመስገን፤ መጥቶ ሕዝቡን ተቤዥቶአልና።

69- በባሪያው በዳዊት ቤት፣ የድነት ቀንድ አስነሥቶልናል፤

70- ይህም ጥንት በቅዱሳን ነቢያቱ አፍ እንደ ተናገረው፣

71- ማዳኑም ከጠላቶቻችንና፣ ከተፃራሪዎቻችን ሁሉ እጅ ነው፤»

- ዘካርያስ የተናገረው ምን ነበር?

- ዘካርያስ እግዚአብሔርን ያመሰግን ነበር።

- ዘካርያስ እግዚአብሔርን ያመሰገነው ለምን ነበር?

- ዘካርያስ ያመሰገነው፥ እግዚአብሔር አዳኙን በቅርቡ እንደሚልክ ስላወቀ ነበር።

- ዘካርያስ ያመሰገነው አዳኙ መጥቶ ሰዎችን ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ኃይል እንደሚያድን ስላወቀ ነበር።

- ሰዎች ሁሉ ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ኃይል መዳን ያስፈልጋቸዋል።
- እግዚአብሔር አዳኙን ወደ ዓለም የላከው ለዚሁ ነበር።

- ዘካርያስ አዳኙ እንደሚመጣና ሕዝቡን ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ኃይል እንደሚያድናቸው በምን አወቀ?

- ዘካርያስ ያወቀው እግዚአብሔር አዳኝ እንደሚልክ የገባውን የተስፋ ቃል ከእግዚአብሔር መጽሐፍ ስላነበበ ነው።

- ዘካርያስ ሌላ ምን ተናገረ?

ሉቃስ 1፡72-75

72- ዘካርያስ እንዲህ አለ «ይህንም ያደረገው ለአባቶቻችን ምሕረቱን ለማሳየት፣ ቅዱስ ኪዳኑን ለማስታወስ፣
73- ለአባታችን ለአብርሃም የማለውን መሐላ ለማሰብ፣
74- ከጠላቶቻችን እጅ አውጥቶ፣ ያለፍርሀት እንድናገለግለው፣
75- በዘመናችንም ሁሉ በቅድስናና በጽድቅ በፊቱ ሊያቆመን ነው።»

- ዘካርያስ እግዚአብሔር አዳኝ ለመላክ የገባውን ቃል ኪዳን እንደሚፈጽም አውቋል።

- ይህ እግዚአብሔር ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ ከብዙ ዘመናት በፊት የገባው ቃል ነበር።

- እግዚአብሔር ሁልጊዜ ቃሉን ይፈጽማል።
- እግዚአብሔር ፈጽሞ ቃሉን አይሽርም።

- ዘካርያስ ስለ ተወለደለት ልጁ ስለ ዮሐንስ ምን ተናገረ?

ሉቃስ 1፡76

76- ዘካርያስ እንዲህ አለ «ደግሞም አንተ ሕፃን ሆይ፤ የልዑል ነቢይ ትባላለህ፤ የጌታን መንገድ ለማዘጋጀት በፊቱ ትሄዳለህና።»

- ዘካርያስ የእርሱ ልጅ ዮሐንስ «የልዑሉ» ነቢይ እንደሚሆን ተናገረ።

- ልዑል ማን ነው?
- ልዑል እግዚአብሔር አብ ነው።

- የዘካርያስ ልጅ ዮሐንስ የሚሠራው ሥራ ምን ነበር?

- ዮሐንስ የጌታን መንገድ ለማዘጋጀት በፊቱ ይሄዳል።
- ዮሐንስ በፊቱ እየሄደ መንገድ የሚያዘጋጅለት ይህ ጌታ ማን ነበር?

- እርሱ ኢየሱስ አዳኙ እግዚአብሔር ነበር።

- ኖኅንና ቤተሰቡን ከጥፋት ውኃ ያዳናቸው ብቸኛው ማን ነበር?
- እግዚአብሔር።

- ይስሐቅን ከሞት ያዳነውና በእርሱ ምትክ የአውራ በግ ያዘጋጀው ማን ነበር?

- እግዚአብሔር።

- እስራኤላውያንን ከግብፅ ከፈርዖን ባርነት ያዳናቸው ብቸኛው ማን ነበር?
- እግዚአብሔር።

- ዮናስን ከዓሣ ነባሪው ሆድ ውስጥ ያዳነው ብቸኛው ማን ነበር?
- እግዚአብሔር።

- እኛን ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ኃይል ሊያድነን የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

- ዘካርያስ ስለ ልጁ ስለ ዮሐንስ ሌላ ምን ተናገረ?

ሉቃስ 1፥77

77- ዘካርያስ እንዲህ አለ «የኃጢአታቸውን ስርየት ከማግኘታቸው የተነሣ፤ ለሕዝቡ የመዳንን ዕውቀት ትሰጥ ዘንድ፣

- ዘካርያስ ዮሐንስ ለሕዝቡ የመዳንን መንገድ ያሳያል አለ።

- ዘካርያስ ዮሐንስ ለሕዝቡ የኃጢአት ዋጋ የሚከፈልበትን መንገድ ያሳያል አለ።

- ዘካርያስ ሌላ ምን ተናገረ?

ሉቃስ 1፥78-79

78- ዘካርያስ እንዲህ አለ «ከአምላካችንም በጎ ምሕረት የተነሣ፣ የንጋት ፀሓይ ከሰማይ ወጣችልን፤

79- ይኸውም በጨለማ ለሚኖሩት፣ በሞት ጥላ ውስጥ ላሉት እንዲያበራና፣ እግሮቻችንንም ወደ ሰላም መንገድ እንዲመራ ነው።»

- የሚመጣው አዳኝ በማለዳ ፀሐይ የተመሰለው እንዴት ነው?

- አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ፡

- የጨረቃም ሆነ የከዋክብት ብርሃን በሌለበት፥ በጣም ጨለማ በሆነ አንድ ሌሊት መንገድ ጠፍቶአችሁ በማይታወቅ ደን ውስጥ ተገኛችሁ እንበል።

- ጨለማምውን በጣም ስለ ፈራችሁት የማለዳ ፀሐይ እስኪወጣላችሁ ድረስ በናፍቆት ትጠባበቃላችሁ።

- አዳምና ሔዋን ኃጢአት በሠሩበት ጊዜ የሕይወታቸው ብርሃን ከሆነው ከእግዚአብሔር ተለዩ።

- በኃጢአታቸው ምክንያት ነፍሳቸው በሰይጣን ጨለማ ውስጥ ገባች።

- በኃጢአት ምክንያት ሰዎች ሁሉ በሰይጣን ጨለማ ውስጥ ተወለዱ።

- የማለዳ ፀሐይ ለድቅድቁ ጨለማ ብርሃን እንደሚሰጥ ሁሉ አዳኙም በሰይጣን ጨለማ ለተዋጠው ሕይወት ብርሃንን ይሰጣል።

- በዓለም ላይ ስንት ፀሐዮች አሉ?
- አንድ ብቻ።

- በዚህ ዓለም አንድ ፀሐይ ብቻ እንዳለች ሁሉ ለእኛ ከሰማይ ብርሃንን የሚሰጥ አንድ አዳኝ ብቻ አለ።

- እግዚአብሔር ለመላክ ቃል የገባው አዳኝ ስንት ነበር?

- አንድ ብቻ።

- ለዓለም ሁሉ ብርሐን የምትሰጠው አንድ ፀሐይ ብቻ እንደ ሆነች ሁሉ እንዲሁ ሁሉንም ሰው ሊያድን የሚችለው አንድ አዳኝ ብቻ ነው።

- እግዚአብሔር ብዙ አዳኞችን ለመላክ ቃል አልገባም።

- እግዚአብሔር አንድ አዳኝ ብቻ ለመላክ ቃል ገባ።

- የዘካርያስ ልጅ ዮሐንስ አደገ፣ በእግዚአብሔርም ላይ ትልቅ እምነት ነበረው።

ሉቃስ 1፡80

80- ሕፃኑም አደገ፤ በመንፈስም ጠነከረ፤ ለእስራኤልም ሕዝብ በይፋ እስከ ታየበት ቀን ድረስ በበረሓ ኖረ።

- ዮሐንስ የመዳንን መንገድ ለሕዝቡ እንዲያሳይ እግዚአብሔር እስኪጠራው ድረስ በበረሓ ኖረ።